# የሃሳብ ልዩነትንና ተቃውሞን ማዳፈን

## በንግግር እና በጽሁፍ ነጻነት ላይ ያነጣጠረ ጥቃት በኢትዮጵያ

AMNESTY INTERNATIONAL



አምነስቲ ኢንተርናሽናል አለም አቀፋዊ ንቅናቄ ሲሆን ከ3 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ደጋፊዎቹ፣ አባላቱ እና ተሳታፊዎቹ በ150 አገራት እና ግዛቶች ውስጥ አስከፊ የሆኑ የሰብአዊ መብቶች ረገጣዎች እንዲቆሙ በመታገል ላይ ይገኛሉ።

አላማችን ለእያንዳንዱ ሰው በአለም አቀፉ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ እና በሌሎች አለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብቶች መመዘኛዎች የተጠበቁት መብቶች ሁሉ እንዲከበሩ ነው።

ከማንኛውም መንግስት፣ ፖለቲካዊ አመለካከት፣ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ወይም ኃይማኖት ገለልተኛ ስንሆን ገቢያችንን በዋናነት የምናሰባስበው ከአባላት መዋጮና ከገለልተኛ የኅብረተሰብ ክፍሎች ከሚገኙ እርዳታዎች ነው።

**AMNESTY**
**INTERNATIONAL**


በመጀመሪያ እ. አ. አ. 2011 ዓ. ም. ታተመ
Amnesty International Ltd
Peter Benenson House
1 Easton Street
London WC1X 0DW
United Kingdom



© የአምነስቲ ኢንተርናሽናል እትመት 2011



የመግለጫው መለያ፡ AFR 25/011/2011 Amharic
ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ የተተረጎመ
በአምነስቲ ኢንተርናሽናል የታተመ፤
ኢንተርናሽናል ሴክሬታሪያት፣ዩናይትድ ኪንግደም



ሁሉም ያሳታሚው የባለቤትነት መብቶች በሕግ የተጠበቁ ናቸው። የዚህ ህትመት የቅጂ መብቶች እንደተጠበቁ ሆነው በማናቸውም መንገድ ይህን እትመት በማባዛትያልክፍያ ግንዛቤ ለማስጨበጫነት፣ ለቅስቀሳ እና ለማስተማሪያ አገልግሎቶች እንዲውል መጠቀም የሚቻል ሲሆን በሽያጭ መልክ ማሰራጨት የተከለከለ ነው። ህትመቱ ከዚህ በላይ ለተጠቀሱት አላማዎች ከዋለ፣ የህትመቱን ጠቀሜታ መገምገም ይቻለው ዘንድ ተጠቃሚዎቹ እንዲያሳውቁት አሳታሚው ይጠይቃል። ከተጠቀሱት ውጭ በሌላ ማንኛውም ሁኔታዎች ወይም ለሌላ እትመት አገልግሎት ለመጠቀም ወይም ለመተርጎም ወይም ለማሳተም በቅድሚያ የአሳታሚው በጽሑፍ የተረጋገጠ ፈቃድ ያስፈልጋል፤ እንዲሁም ክፍያም ሊጠይቅበት ይችላል። ፈቃድ ለመጠየቅ ወይም ለማንኛውም ተጨማሪ መረጃ የሚከተለ አድራሻ ይጠቀሙ። copyright@amnesty.org


**የሽፋን ምስል፡** በበርካታ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትና ጋዜጠኞች ላይ የቀረቡት የወንጀል ክሶች የሚሰሙበት የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሕንጻ።
© አፕ/ፕአ

**amnesty.org**



# ለመርዳት እፈልጋለሁ

**ከአምነስቲ ኢንተርናሽናል** በከፍተኛ ሁኔታ በሚታወቁ ግጭት ያለባቸው ሥፍራዎችም ሆነ በተረሱ የአለማችን ክፍሎች ፍትሕ፣ ነጻነት እና ተገቢው ክብር ለሰው ልጆች ሁሉ እንዲሆን ቅስቀሳ የሚያደርግ ሲሆን የተሻለ ዓለምን ለመገንባት የሚያስችል የሕዝብ ተሳትፎ እንዲኖርም ያበረታታል።

## ምን ማድረግ ይኖርብዎታል?

በመላው አለም የሚታዩት ሕዝባዊ እንቅስቃሰዎች የሚያሳዩት ሰብአዊ መብቶችን የሚያኮስሱ አደገኛ ኃይሎችን ማስቆም የሚቻል መሆኑን ነው። የእዚህ እንቅስቃሴ አካል ይሁኑ። ፍርሃትንና ጥላቻን የሚዘሩትንም ይታገሏቸው።

- ከአምነስቲ ኢንተርናሽናል ጋር አብረው በመቆም የሰብዓዊ መብቶች እረገጣ እንዲያከትም የሚካሄደው አለም ዓቀፍ ንቅናቄ አካል ይሆኑ። ለውጥ እንድናመጣ ይደግፉን።
- የአምነስቲ ኢንተርናሽናልን ሥራ ለማገዝ እርዳታዎን ይለግሱ።

## ተባብረን ድምጻችን ተሰሚ እንዲሆን ለማድረግ እንችላለን።

☐ የአምነስቲ ኢንተርናሽናል አባል በመሆን ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት ፍላጎት አለኝ

ሥም

አድራሻ

አገር

ኢ-ሜል

☐ ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል የገንዘብ እርዳታ ማድረግ እፈልጋለሁ (የገንዘብ እርዳታው በፓውንድ፣ በአሜሪካ ዶላር ወይም በዩሮ ሊሆን ይችላል)

የገንዘቡ መጠን

ከሚከተለው ካርዴ ተከፋይ ይሁን ቪዛ ☐ ማስተር ካርድ ☐

የካርድ ቁጥር

የአገልግሎት ጊዜው ማብቂያ

ፊርማ

ይህን ቅጽ ከሞሉ በኋላ በሚገኙበት አገር ለሚገኝ የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ጽ/ቤት ያስረክቡ።

የሌሎች የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ጽ/ቤቶችን አድራሻ ለማግኘት፡
www.amnesty.org/en/worldwide-sites
በሚኖሩበት አገር የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ጽ/ቤት ከሌለ ቅጹን በሚከተለው አድራሻ ይላኩ፡

**Amnesty International**, International Secretariat, Peter Benenson House,
1 Easton Street, London WC1X 0DW, United Kingdom

amnesty.org

# የሃሳብ ልዩነትንና ተቃውሞን ማዳፈን

## በንግግር እና በጽሁፍ ነጻነት ላይ ያነጣጠረ ጥቃት በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ በርካታ ቁጥር ያላቸው የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት እና ጋዜጠኞች ሕጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ በመንግስት ላይ በሚሰነዝሩት ትችት ሳቢያ በ2011 ዓ.ም. ተይዘው ለእስር ተዳርጋዋል።

እንደ አምነስቲ ኢንተርናሽናል እምነት መንግስት ሽብርተኝነትን ለመዋጋት በሚል ያዘጋጀውን ድንጋጌ የተቃውሞ ሃሳቦችን ለማፈኛነት እየተጠቀመበት ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ መንግስትን የሚነቅፉ ሰዎችን ማሰርና በወንጀል መክሰስ አዲስ ክስተት አይደለም። ይሁንና የእስራቱ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ መሄድ የሚያመለክተው 2011 ዓ.ም. በንግግርና በጽሑፍ ነጻነት ላይ ያነጣጠረ የተፋፋመ ጥቃት መሰንዘሩን ነው።

በታሳሪዎቹ የተደረጉ የሰላማዊ ተቃውሞ ጥሪዎች፤ እንዲሁም የተጻፉ መጣጥፎችና ግጥሞች ለሽብርተኝነት እና ለአገር ክህደት የወንጀል ክሶች እንደማስረጃነት መቅረባቸው የሚጠቁመው የንግግርና የጽሑፍ ነጻነትን መጠቀም የሚያስወነጅል መሆኑን ነው።

በእስር ላይ ሆነው ፍርድ በመጠባበቅ ላይ የሚገኙት ግለሰቦች ማሰቃየትና ለሎች በደሎችን፤ እንዲሁም ተገደው ቀድሞ በተዘጋጀ የእምነት ቃል መግለጫ ሰነድ ላይ እንዲፈርሙ፣ እና ከጠበቆቻቸውና ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንዳይገናኙ መከልከልን ጨምሮ ለሌሎች የሰብአዊ መብቶች እረገጣዎች ተዳርገዋል። መንግስት ታሳሪዎቹ ወንጀለኞች ናቸው በሚል በይፋ የሰጠው አስተያየትም ተከሳሾቹ ፍትሃዊ የሆነ ዳኝነት አያገኙም የሚለውን ስጋት እጅግ ከፍ እንዲል አድርጎታል። አምነስቲ ኢንተርናሽናልም የፍርዱ ሂደቱን ጥንቃቄ በተሞላው መልኩ የአለም አቀፍ ማህበረሰቡ እንዲከታተል ጥሪ ያደርጋል።

እነዚህ ክስተቶች የተለዩ አስተሳሰቦችን ለሚያራምዱ ወይም ገለልተኛ የሆነ የፖለቲካ አመለካከትን ለማንጸባረቅ የሚሞክሩትን ሁሉ አርፈው እንዲቀመጡ፤ ካለበለዚያም የመታሰር አደጋ የሚገጥማቸው መሆኑን የሚያሳስብ የማስፈራሪያ መልክት ነው። መንግስት እንደጠቆመውም የጥቃት ዘመቻው ያልተጠናቀቀና ሌሎችን ማሰሩም የሚቀጥል መሆኑን ነው።

የኢትዮጵያ ባለስልጣናትም በአገሪቱ ወስጥ ተሟጦ የቀረውን የንግግርና የጽሑፍ ነጻነት ጨርሶ ለማጥፋት ቆርጠው መነሳታቸውን አሳይተዋል። አምነስቲ ኢንተርናሽናል የኢትዮጵያ መንግስት በሰላማዊ መንገድ ነጻ አመለካከታቸውን የሚያራምዱ ሰዎችን መብት እንዲያከብርና በዚህም ሳቢያ የታሰሩትን ሰዎች በአፋጣኝ እንዲፈታ ያሳስባል።

amnesty.org

የመግለጫው መለያ፡ AFR 25/011/2011
ታህሳስ 2011

AMNESTY INTERNATIONAL